# የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት ለመስጠት የወጣ መመሪያ ቁጥር 46/2002

በጉምሩክ ሥራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በሕዝብና በመንግሥት ጥቅም ላይ የሚያደርሱት ጉዳትና የአፈፃፀም ባህሪያቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት እንዲያገኙ ለማድረግ ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 622/01 በአንቀፅ 107 ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፣

በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት የሚሰጥባቸውን በጉምሩክ ሥራ ላይ የሚፈፀሙ የወንጀል ዓይነቶች፣ የሚወሰዱ የቅጣት እርምጃዎች፣ እና በዐቃቤ ሕግ የአያስከስስም ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች በአስተዳደራዊ ውሳኔ የሚታዩበት ሁኔታ እንዲሁም የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 107/2/፣ አንቀፅ 112/2/ እና የባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀፅ 6/19/፣ 20/2/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል 1

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት ለመስጠት የወጣ መመሪያ ቁጥር 46/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፡-

1. "አስተዳደራዊ ውሳኔ" ማለት የጉምሩክ ሥራን በኃላፊነት እንዲያከናውን በተመደበ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ወይም ኮሚቴ በጉምሩክ ጉዳዮች ላይ የሚሰጥ ውሳኔ ሲሆን በባለሥልጣኑ ዐቃቤያነ ሕግ የሚሰጡ ውሳኔዎችን አይጨምርም፡፡
2. " አቤቱታ" ማለት በአስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታ ነው፡፡
3. "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡

4. "አቤቱታ አጣሪ ቡድን" ማለት በባለሥልጣኑ የሚቋቋም የጉምሩክ የቅሬታ ሰሚ አካል ነው፡፡
5. "ልዩነት" ማለት በተፈፀመው የጉምሩክ ወንጀል ለተያዘው ዕቃ በተከፈለው እና በትክክል ሊከፈል በሚገባው ቀረጥና ታክስ መካከል ያለው የገንዘብ መጠን ልዩነት ነው፡፡
6. "ዐቃቤ ሕግ" ወይም "የዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት" ማለት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዐቃቤ ሕግ ወይም የዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት ነው፡፡
7. ሌሎች ቃላት እና ሐረጐች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ላይ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በክፍል ሁለት ተለይተው በተዘረዘሩት የጉምሩክ ወንጀሎች ላይ ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥባቸው የጉምሩክ ወንጀሎች ዓይነት እና የቅጣት እርምጃዎች</u>

## 4. <u>መርህ</u>

1. የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አሟልቶ ወደ አገር ውስጥ በገባው ዕቃ ላይ የተገኘው ልዩነት ከተከፈለው ቀረጥና ታክስ ጋር ሲነፃፀር ከብር 500,000 ያልበለጠ ከሆነ ወይም ፤

2. የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አሟልቶ ወደ አገር ውስጥበገባው ዕቃ ላይ የተገኘው ልዩነት ከብር 500,000 በላይ ሆኖ ነገር ግን አስቀድሞ ከተከፈለው የቀረጥና ታክስ መጠን ጋር ሲነፃፀር ከ25 በመቶ የማይበልጥ የሆነ እንደሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት ይታያል፡፡

## 5. <u>የማጭበርበር ወንጀሎች እና የቅጣት እርምጃዎች</u>

1. ማንኛውም ሰው ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት ዕቃ በልዩነት የተገኘበት እንደሆነ ለዕቃው የሚከፈለው ቀረጥ እና ታክስ መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በትርፍነት

/ከሰነድ ውጪ/ ተቀላቅሎ ለገባው ዕቃ የሚከፈለውን ቀረጥ እና ታክስ በሁለት ተባዝቶ የሚገኘውን የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

2. ማንኛውም ሰው በሕጋዊ ዕቃ ከለላነት በማናቸውም ሁኔታ ገደብ የተደረገበትን ዕቃ ወደ አገር እንዲገባ ያደረገ ወይም ያስደረገ ወይም ለማስገባት የሞከረ ወይም ወደአገር አስገብቶ የተገኘ እንደሆነ እና ገደብ የተደረገበት ዕቃ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ካገኘ ገደብ እንዳልተደረገበት ዕቃ ተቆጥሮ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 በተመለከተው የገንዘብ ቅጣት ስሌት መሰረት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 6. ሌሎች የማጭበርበር ወንጀሎች

1. ማንኛውም ሰው በስሪት አገር ላይ ተመስርቶ መከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዳይከፈል፣ ወይም አሳንሶ ለመክፈል ወይም ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ለማድረግ በማናቸውም ሁኔታ ማጭበርበር የፈፀመ ወይም ለማጭበርበር የሞከረ እንደሆነ በስሪት አገር ማሳሳት የተፈፀመበት ወይም ማሳሳት ሊፈፀምበት የነበረው እቃ በትርፍነት እንደመጣ ተቆጥሮ ላስገባው ዕቃ በሙሉ መክፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ በትርፍነት ለመጣው ዕቃ መከፈል የሚገባው ቀረጥ እና ታክስ በሁለት ተባዝቶ የሚገኘውን የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
2. አግባብ ካለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያገኙ የውጭ እና የሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ለሚያካሂዱአቸው የኢንቨስትመንት ሥራዎች እና ለግል መገልገያ የሚያስፈልጓቸው መሳሪያዎችና ዕቃዎች ከተፈቀደላቸው መጠን በላይ ወይም ውጭ በልዩነት እስከ 25% አስገብተው ሲገኙ በልዩነት በገባው እቃ ላይ የሚከፈለው ቀረጥ እና ታክስ እንደተጠበቀ ሆኖ ይኸው የገንዘብ መጠን በሁለት ተባዝቶ የሚገኘውን የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

3. በውጭ አገር ለአንድ ዓመትና ከአንድ ዓመት በታች ቆይተው ወደ ሀገራቸው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን ወይም ትውልደ ኢትዮጵያውያን ተጓዦች በሕግ ከተፈቀደላቸው መጠን በላይ በትርፍነት ያስመጡት እቃ ሊከፈልበት የሚገባው ቀረጥ እና ታክስ መጠን ከብር 20,000 ሺ ካልበለጠ እና የተከለከለ እቃ ካልሆነ

በትርፍነት የገባው ዕቃ ላይ የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ እንደተጠበቀ ሆኖ ይኸው የገንዘብ መጠን በሁለት ተባዝቶ የሚገኘውን የገንዘብ ቅጣት እንዲከፈሉ ይደረጋል፡፡

4. በውጭ አገር ከአንድ ዓመት በላይ በተለያዩ ምክንያቶች ቆይተው ወደ ሀገራቸው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን ወይም ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወይም ወደ ኢትዮጵያ ለተለያዩ ጉዳዩች የሚመጡ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ተጓዦች በሕግ ከተፈቀደላቸው በላይ በትርፍነት ያስገቡት እቃ የቀረጥና ታክስ መጠን ከብር 30,000 ያልበለጠ ከሆነ እና ክልክላ ያልተደረገበት እቃ ከሆነ በትርፍነት በተገኘው እቃ ላይ የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ እንደተጠበቀ ሆኖ ይኸው የገንዘብ መጠን በሁለት ተባዝቶ የሚገኘውን የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

## 7. <u>ከቀረጥ ነፃ በገባ ዕቃ አላግባብ መገልገል</u>

1. ማንኛውም ሰው በጉምሩክ አዋጅ አንቀፅ 98/1/ /ሀ/ ወይም /ለ/ ላይ የተደነገገውን ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ዕቃው በተላለፈ ጊዜ በዕቃው ላይ መከፈል የሚገባው ቀረጥ እና ታክስ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥ እና ታክሱን 25% መቀጫ በማስከፈል ዕቃው እንዲለቀቅ ይደረጋል፡፡
2. ዕቃው የተላለፈበትን ትክክለኛ ጊዜ ማወቅ ካልተቻለ ዕቃው ወደ አገር የገባበትን ጊዜ ወይም ወደ አገር ገብቷል ተብሎ የሚገመትበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ ቀረጥና ታክሱን እንዲሁም የገንዘብ መቀጮውን እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 8. <u>ሕግን በመተላለፍ የውጭ ምንዛሪ እና ብርን ከሀገር ስለማስወጣት እና ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት</u>

1. ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ ወይም ነዋሪ የሆነ ሰው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያን በመተላለፍ ከ10,000 የአሜሪካን ዶላር ያልበለጠ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ሌላ ዓይነት የውጭ ምንዛሪ ከአገር ለማስወጣት ወይም በሕገወጥ መንገድ ወደአገር ለማስገባት ሲሞክር የተገኘ እንደሆነ ይኸው በትርፍነት የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

2. ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ዜጋ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያን በመተላለፍ ከ5,000 የአሜሪካን ዶላር ያልበለጠ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ሌላ ዓይነት የውጭ ምንዛሪ ከአገር ለማስወጣት ወይም በሕገወጥ መንገድ ወደአገር ለማስገባት ሲሞክር የተገኘ እንደሆነ ይኸው በትርፍነት የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
3. ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያን በመተላለፍ ከብር 3,000 /ሦስት ሺ/ ያልበለጠ ይዞ ከአገር ለማስወጣት ወይም በሕገወጥ መንገድ ወደአገር ለማስገባት ሲሞክር የተገኘ እንደሆነ ይኸው በትርፍነት የተገኘው ብር ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
4. ማንኛውም ሰው ከዚህ በላይ በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 1 ወይም በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 2 ከተመለከተው የውጭ ምንዛሪ በላይ ወይም በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ ከተመለከተው የብር መጠን በላይ ይዞ ከአገር ሲወጣ ወይም ወደአገር ሲገባ የተገኘ እንደሆነ የምርመራ መዝገብ ተደራጅቶ ለዐቃቤ ሕግ ይላካል፡፡ የተያዘው የውጭ ምንዛሪ ወይም ብር በኤግዚቪትነት ተመዝግቦ ይዞ ለተገኘው ሕጋዊ ደረሰኝ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡
5. ለመንግሥት ገቢ የሚደረገው ብር ወይም የውጭ ምንዛሪ ዓይነቱ፣ የኖቱ ቁጥር እና የደረሰኙ ቁጥር ለዚሁ በተዘጋጀ መዝገብ እንዲመዘገብ ተደርጐ ገንዘቡን ይዞ ለተገኘው ሰው ደረሰኝ ይሰጠዋል፡፡
6. ከዚህ በላይ በቅጣት መልክ ለመንግሥት ገቢ የሚደረገው ወይም በኤግዚቢትነት የተመዘገበው ብር ወይም የውጭ ምንዛሪ ቢበዛ በ48 ሰዓት ውስጥ ወደ ተገቢው የባንክ አካውንት ገቢ ይደረጋል፡፡ ይኸውም ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ እና ለሕግ ማስከበር እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ሪፖርት ይደረጋል፡፡
7. “በሕግ ያልተፈቀደ” ማለት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ /ሕግ/ ያልተፈቀደ ማለት ነው፡፡

## 9. ማስታወቂያ የማስነገር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ከአገር ሲወጣ ወይም ወደአገር ሲገባ ስለሚይዘው በሕግ የተፈቀደ የውጭ ምንዛሪ ወይም የብር መጠን ወደአገር መግቢያና ከአገር መውጭያ በሮች በድምፅ፣ በምስልና በጽሑፍ በተደገፈ አማርኛን ጨምሮ በተለያዩ አለም አቀፍ ቋንቋዎች በባለሥልጣኑ የትምህርትና ግንኙነት የሥራ ሂደት መነገር አለበት፡፡

## 10. ሕገ ወጥ እቃዎችን በቅን ልቦና ይዞ መገኘት

1. በሕግ የባለቤትነት ማስረጃ የመስጠት ሥልጣን ካለው አካል የተሰጠን ማስረጃ መሠረት አድርጎ የጉምሩክን ሕግ በመተላለፍ ወደ ሀገር የገባን ዕቃ በቅን ልቦና ባለቤት ለመሆን አስቦ ይዞ የተገኘ ሰው ለዕቃው ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ዕቃው ይለቀቅለታል፡፡
2. በቅን ልቦና ዕቃውን የያዘው ሰው ቀረጥና ታክሱን ካልከፈለ የተያዘው ሕገወጥ ዕቃ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

## 11. የጉምሩክ መጋዘን እንዲያቋቁም የተፈቀደለት ሰው ግዴታን ስለመጣስ

የጉምሩክ መጋዘን እንዲያቋቁም የተፈቀደለት ባለፈቃድ በአዋጅ ቁጥር 622/2001፡-

1. በአንቀፅ 76 /ሀ/ /ለ/ /ሐ/ /ሰ/ እና /ቀ/ ላይ የተዘረዘሩትን ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ብር 50,000 /ሃምሳ ሺ/ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
2. በአንቀፅ 76/መ/ /ሠ/ /ረ/ እና /ሸ/ ላይ የተዘረዘሩትን ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ብር 70,000 /ሰባ ሺ/ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
3. በአንቀፅ 76 ሥር ከተዘረዘሩት ግዴታዎች መካከል በአንድ ጊዜ ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑትን ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺ/ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 12. በተደጋጋሚ ጥፋቶች ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ

1. ጥፋቱ ለሁለተኛ ጊዜ ተፈፅሞ የተገኘ እንደሆነ በሚጣልበት ቅጣት ላይ የቅጣቱን 50 በመቶ በመጨመር እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

2. ጥፋቱ ለሦስተኛ ጊዜ ተፈፅሞ የተገኘ እንደሆነ የሚጣልበት ቅጣት ላይ የቅጣቱን 75 በመቶ በመጨመር እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
3. ለአራተኛ ጊዜ እና ከዚያ በላይ ጥፋት የፈፀመ ሰው የቅጣቱን 100 ፐርሰንት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
4. ለዚህ አንቀፅ አፈፃፀም አንድ ጥፋት ተደጋጋሚ ጥፋት ነው ተብሎ የሚመዘገበው በልዩነት የተገኘው የቀረጥና ታክስ መጠን ከ10% /ከአሥር በመቶ/ የበለጠ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ሥነ ሥርዓቶች

## 13. በዐቃቤ ሕግ የአያስከስስም ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ስለሚጣል አስተዳደራዊ ቅጣት

ዐቃቤ ሕግ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀፅ 42 መሠረት የአያስከስስም ወይም የመዝጋት ውሳኔ ሲሰጥ ጉዳዩ በዚሁ መመሪያ መሠረት በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲስተናገድ ወደሚመለከተው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይልካል፡፡

## 14. እቃን ስለመያዝና ስለመልቀቅ

1. በዚህ መመሪያ አስተዳደራዊ ውሳኔ በሚሰጥባቸው ጉዳዮች በትርፍነት ወይም በልዩነት ወይም በሽፋንነት ወይም በከለላነት እና በመሳሰሉት የመጡ ማናቸውም እቃዎች በሙሉ በጉዳዩ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ተይዘው ይቆያሉ፡፡

2. በጉዳዩ የቅጣት ውሳኔ ከተሰጠ እና
   ሀ. ተቀጭው የሚፈለግበትን የቀረጥና ታክስ እና የተጣለበትን ቅጣት ከከፈለ የተያዘው እቃ ወዲያውኑ ይለቀቅለታል፣ ወይም
   ለ. ተቀጭው በተሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅሬታ ኖሮት አቤቱታ የሚያቀርብ መሆኑን በመግለፅ እና የተቃውሞውን ነጥብ በማስመዝገብ የሚፈለግበትን ቀረጥና ታክስ እና የቅጣት ገንዘብ በመክፈል የተያዘበትን እቃ በሙሉ ማስለቀቅ ይችላል፡፡

3. በዚሁ መመሪያ በአንቀፅ 14 /2/ /ለ/ ላይ በተመለከተው መሠረት ሕግ ተላላፊው የተቃውሞ ነጥብ አስመዝግቦ የሚፈለግበትን ቀረጥና ታክስ እንዲሁም መቀጫ ያልከፈለ እንደሆነ የተያዘው እቃ በሙሉ በጉምሩክ አዋጅ የእቃ አወጋገድ ሥርዓት መሠረት ሊወገድ ይችላል፡፡

## 15. ስለውሳኔ አሰጣጥ እና ማሳወቅ

1. የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት መተላለፍ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቡድን በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ አግባብነት ያላቸው ሰነዶች እና ማስረጃዎች በቀረቡለት በ7 ቀናት ውስጥ በመመሪያው መሰረት ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
2. በዚህ መመሪያ መሰረት የሚሰጡ ማናቸውም ውሳኔዎች ወይም ትእዛዞች ጉዳዩ ለሚመለከተው ሰው በጽሑፍ መሰጠት አለባቸው፡፡ የቅጣት ማሳወቂያ ቅጽ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ ቁጥር 1 መሠረት መሆን አለበት፡፡
3. ተቀጪው የቅጣት ውሳኔው በፅሁፍ በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ የቅጣት ክፍያውን መፈፀም አለበት፡፡

## 16. ልዩነትን ስለመመዝገብ

በዚህ መመሪያ መሠረት አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጡ የባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ውሳኔ በሰጡባቸው ጉዳዩች የተገኘውን የቀረጥና ታክስ ልዩነት ሌሎች የባለሥልጣኑ ጽ/ቤቶች መረጃውን ሊያገኙ በሚችሉበት ሁኔታ በአሲኩዳ ወይም ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀ የአውቶሜሽን ሲስተም መረብ በተመዘገቡበት ዲክላራሲዮን በመለየት በጥንቃቄ የመመዝገብ ግዴታ አለባቸው፡፡

## 17. ሪፖርት ስለማድረግ

የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት መተላለፍ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቡድንና የሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት በዚህ መመሪያ መሠረት ውሳኔ የተሰጠባቸውን ጉዳዩች መዝገብ ያደራጅሉ በየወሩም ለመረጃ ምርመራና ሥጋት ሥራ አመራር ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

## 18. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጐች</u>

የጉምሩክ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ ለመጨረስ ወጥቶ የነበረው መመሪያ ቁጥር 12/2001 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡ በዚህ መመሪያ በሚታዩ ጉዳዮች ላይ አስቀድመው የነበሩ አሰራሮችና ልማዶች ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ከሆኑ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 19. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ከመፅናቱ በፊት ተጀምረው እልባት ወይም ውሳኔ ያላገኙ በመመሪያው ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት ውሳኔ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

## 20. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት 13 ቀን 2002 ዓ.ም.

መላኩ ፋንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር

<u>አስተዳዳራዊ ውሳኔ ማሳወቂያ ቅጽ</u>

•ሁሉም ክፍት ቦታዎች መሞላት አለባቸው

1. የዕቃው ባለቤት ስም ከነአያቱ /የድርጅቱ ስም/፣…………………………………….

2. አድራሻ፣ ………………………………

3. የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አስፈፃሚ ስም፣ ……………………………..

4. የዲክላራሲዮን ቁጥር፣ ……………………………….

5. የንግድ ፈቃድ ቁጥር፣ ……………………የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር …………...

6. አስቀድሞ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ መጠን ብር ……………………./……………

7. የተገኘው የቀረጥና ታክስ ልዩነት

   7.1 በብር ……………………………../……………………………/

   7.2 በመቶኛ …………………………../……………………………./

8. የተፈፀመው የጉምሩክ ወንጀል ዓይነት

   …………………………………………………………………………………

   ………………………………………………………………………………..

9. የተፈፀመው ጥፋት

   - ☐ 1ኛ ጥፋት
   - ☐ 2ኛ ጥፋት
   - ☐ 3ኛ ጥፋት
   - ☐ 4ኛና ከዚህ በላይ

10.የተሰጠ ውሳኔ

   …………………………………………………………………………………

   ………………………………………………………………………………..።

9. ሰነዱን የመረመረው ሠራተኛ፣ ስም፣………………………………..

   ፊርማ፣ ……………………………

   ቀን፣ ………………………

10. ያረጋገጠው ኃላፊ ስም፣ ………………………………

   ፊርማ፣ ……………………………

   ቀን፣ ……………………………….

<u>ማሳሰቢያ</u>

በዚህ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው ውሳኔው በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ ለአቤቱታ አጣሪ ቡድን ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።